የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር

የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ

ሕዳር 2018 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ኢትዮጵያ

የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር
የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ

<u>አንቀጽ አንድ</u>
<u>የዚህ ሠነድ ዓላማ</u>

ጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር (ከዚህ በኋላ “አክሲዮን ማህበር” ወይም “ባንኩ” እየተባለ የሚጠቀስ) በ1952 ዓ.ም በወጣው የንግድ ሕግ መሠረት በ14/11/2013 ዓ.ም በቁጥር ቅ10/249/4U/2013 እና ቅ10/250/4U/2013 በተመዘገቡ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ በ2013 ዓ.ም. የተመሠረተ ነዉ።

በ2013 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ (ከዚህ በኋላ “የንግድ ሕጉ” ተብሎ የሚጠቀስ) የመተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ይታወቅ የነበረውን ሠነድ በተመለከተ በግልጽ ዕውቅና ባለመስጠቱ እና በ1952 ዓ.ም የወጣው የንግድ ሕግ ላይ በመተዳደሪያ ደንብ ላይ እንደሚወሰኑ የተጠቀሱ ጉዳዮችን በመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ እንደሚወሰኑ በመደንገጉ፣ ባንኩ የመተዳደሪያ ደንቡን ከመመሥረቻ ጽሑፉ ጋር በማዋሃድ፣ የንግድ ህጉ ካመጣቸው ሌሎች ለውጦች ጋር በማስማማት እና ነባራዊ ለውጦችን በማካተት የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ ነባሩን የመመሥረቻ ፅሑፍ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም፣የባንኩ የባለአክሲዮኖች 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህንን የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ አጽድቋል።

ይህ ሰነድ **"የጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ"** ተብሎ ይጠራል።

(በዚህ ሠነድ ውስጥ አግባብነት ሲኖረዉ በወንድ ፆታ የተገለጸው ለሴት ፆታ፣ በነጠላ ቁጥር የተገለጸዉ ለብዙ፣ በብዙ ቁጥር የተገለጸው ለነጠላ ቁጥር ያገለግላል)

<u>አንቀጽ ሁለት</u>
<u>የአክሲዮን ማህበሩ ስም</u>

የአክሲዮን ማህበሩ **"ጎሕ ቤቶች ባንክ አክሲዮን ማህበር"** በመባል ይታወቃል።

<u>አንቀጽ ሦስት</u>

<u>የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፣ ቅርንጫፎች እና ተቀጥላ ማህበር</u>

3.1 የባንኩ ዋና መ/ቤት አድራሻ ኢትዮጵያ፣ አዲስ አበባ ከተማ፣ በሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 02፤ የመልዕክት ሣጥን ቁጥር 1704፣ ኢ-ሜል፡ info@gohbetbank.com ሲሆን አድራሻው እንደ አስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል።

3.2 ባንኩ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርጫፎች ያሉት ሲሆን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ቅርንጫፎችና ንዑስ ቅርጫፎችን ሊከፍትና እንዲሁም ተቀጥላ ማህበር (Subsidiary) ሊያቋቁም ይችላል፡፡

አንቀጽ አራት
የአክሲዮን ማህበሩ የንግድ ሥራ ዓላማዎች

የአክሲዮን ማህበሩ በሀገሪቱ ህጎች መሰረት የባንክ ንግድ ሥራ ተብለዉ የሚታወቁትን የንግድ እንቅስቃሴዎች ያከናውናል፡፡ ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝር የንግድ ሥራዎች ያከናውናል፡፡

4.1 ልዩ ልዩ ተቀማጭ ገንዘቦችን ማሰባሰብ፤

4.2 በተጠየቀ ጊዜ የሚከፈሉ ሒሣቦችን፣ በጊዜ ገደብ የሚቀመጡ ሂሳቦችንና ሌሎች የባንክ ሒሣብ መክፈትና ተቀማጭ ገንዘቦች መቀበል፤

4.3 የተለያዩ ብድሮችንናተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት፤

4.4 የወጪና የገቢ ንግድን ፋይናንስ ማድረግ፣ የዓለም አቀፍ ባንኪንግ ሥራና የሐዋላ አገልግሎት መስጠት፤

4.5 የውጭ ሀገር ገንዘቦችን መግዛት፣መያዝ፣መሸጥ፣መመንዘር እንዲሁም የውጭ ምንዛሪንና ከውጭ ምንዛሪ ጋር የተያያዙ ሥራዎችን ማከናወን፤

4.6 የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት፣ አስፈላጊ ሲሆን የክፍያ ሥርዓት ኦፕሬተር አገልግሎትን መስጠት፤

4.7 ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት መስጠትና ተያያዥ ሥራዎችን ማከናወን፤

4.8 የወኪል የባንክ አገልግሎት መስጠት፣

4.9 የቅድሚያ ክፍያ፣ የመልካም ሥራ አፈጻጸም፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናን ጨምሮ የዋስትና ሠነዶችን ማዉጣት፣ ማስተላለፍ፣መነገድ፤

4.10 የንግድ፣ የተስፋ እና የሐዋላ ሰነዶችና የመሳሳሉ የሚተላለፉ ሰነዶችን ማዉጣትና መገበያየት፣

4.11 በውጭ ሀገርም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ተከፋይ የሆኑ የንግድ ሰነዶችን ማዉጣት፣ መቀበል፣ መግዛት፣ መሸጥ፣ ቅናሽ ማድረግ እና የመሳሳሉ ሥራዎችን መስራት፤

4.12 በመንግስትም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚወጡ የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶችንና ወረቀቶችን መቀበል፣ መግዛት፣ መሸጥ፣ቅናሽ ማድረግ(discounting)፤

4.13 በሌሎች ንግድ ማህበራት አክሲዮን፣ ስቶክ እና የዕዳ ሰነድ መግዛትና መገበያየት፣ ሕግ በሚፈቅደዉ መሠረት ኢንቨስት ማድረግ፤

4.14 በካፒታል ገበያና በአክሲዮን ገበያ ውስጥ በመሳተፍ ማናቸውንም የፋይናንስ ሠነዶች መግዛት፣ መሸጥ እና አገልግሎቶች መስጠት፤

4.15 ሠነዶችን፣ ዕንቁዎችን፣ የከበሩ ማዕድናትን፣ ሌሎች ዋጋ ያላቸው ንብረቶችን ወይም ዕቃዎችን ተቀብሎ በአደራ ማስቀመጥ፤

4.16 የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረት መግዛት፣ መከራየት፣ ማከራየትና መሸጥ፤ እንዲሁም አግባብነት ባለዉ ሕግ መሠረት ለንግድና ለመኖሪያ የሚሆኑ ቤቶችን መግዛት፣መገንባት፣ ማከራየት እና መሸጥ፤

4.17 ደንበኞችን በመወከል የኢንቨስትመንት ፈንዶችን ማስተዳደር፤ እንደአስፈጻሚና ባለአደራ መስራት፤

4.18 ከባንኩ አገልግሎቶች ጋር በተያያዘ የማማከር አገልግሎት መስጠት፤

4.19 ሌሎች ከባንክ ሥራ ጋር ተዛማጅነት ያላቸዉን አገልግሎቶች መስጠት፤

አንቀጽ አምስት
የአክሲዮኖች ዓይነትና መደብ

የባንኩ አክሲዮኖች እኩል ዋጋና አንድ ዓይነት መደብ ያላቸዉ፣ ሙሉ ለሙሉ በጥሬ ገንዘብ የተከፈሉ፣ የተመዘገቡና ተራ አክሲዮኖች ናቸው፡፡

አንቀጽ ስድስት
የባንኩ አክሲዮን ላይ የተጻፈ ዋጋ እና ዋና ገንዘብ(ካፒታል)

6.1 የባንኩ የተፈረመ ካፒታል ብር ___________.00 (____________) ነው፡፡

6.2 ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈረመ ዋና ገንዘብ እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) የተጻፈበት ዋጋ ባላቸው ________(_______) ተራ አክሲዮኖች የተከፋፈለ ነው፡፡

6.3 ከተፈረመው ካፒታል ውስጥ ብር ________.00 (___________) በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ ነዉ፡፡

አንቀጽ ሰባት
የአክሲዮን ይዞታ ገደብ

ማንኛውም ሰዉ ብቻዉንም ሆነ ከሌሎች ጋር በጋራ (በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ) ከባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ሊኖረዉ የሚችለዉ ከፍተኛ የአክሲዮን ባለቤትነት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ በሕግ የሚወሰነዉን መጠን ያህል ብቻ ይሆናል፡፡

አንቀጽ ስምንት
የአክሲዮኖች ዋጋ መክፈልና ዋጋቸው ላልተከፈለ አክሲዮኖች ስለሚኖር ኃላፊነት

8.1. የባንኩ ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን ለመግዛት በፈረሙ ጊዜ ቢያንስ የተፈረሙትን አክሲዮኖች 25% (ሃያ አምስት በመቶ)ወዲያውኑ መክፈል አለባቸው። ሆኖም አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔው አዲስ አክሲዮን ግዢ በሚፈፀምበት ጊዜ ወዲያውኑ መከፈል የሚኖርበትን የገንዘብ መጠን ከ25% በመጨመር ሊወስን ይችላል።

8.2. ተፈርሞ ያልተከፈለ ቀሪ የአክሲዮን ዋጋ የሚከፈልበትን ጊዜ ካፒታል እንዲያድግ የወሰነዉ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚወስነዉ ይሆናል።

8.3. አክሲዮን ለመግዛት የፈረሙ ሰዎች፣ ቀደም ሲል አክሲዮን ተላልፎላቸው የነበሩ ሰዎች እንዲሁም የባንኩ ነባር ባለአክሲዮኖች ለፈረሟቸዉ አክሲዮኖች ያልተከፈለውን ቀሪ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው።

8.4. አክሲዮኖች በአላባ ጥቅም የተሰጡ እንደሆነ፤ ባለአላባው የአላባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንዲመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ተፈርሞ ያልተከፈለ የአክሲዮን ገንዘብ እንዲከፈል ጥሪ በሚደረግበት ጊዜ ያልተከፈለዉን ቀሪ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት።

8.5. ዋጋቸው ላልተከፈለባቸዉ አክሲዮኖች ቀሪ ሂሳብ እንዲከፈል ጥሪ ከተደረገ በኃላ በጥሪዉ በተሰጠዉ ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለ በንግድ ሕጉ አንቀጽ 289 ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 7 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ ዘጠኝ
የባለአክሲዮኖች እና ያሏቸዉ አክሲዮኖች ዝርዝር ሁኔታ

ይህ ሰነድ ሲዘጋጅ ያሉትን የባንኩ ባለአክሲዮች ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የፈረሙት የአክሲዮን ብዛትና የከፈሉት የገንዘብ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ የተሻሻለ የመመሥረቻ ጽሑፍ ጋር አባሪ ሆኗል።

አንቀጽ አሥር
የባለአክሲዮኖች መብቶች

አግባብ ባላቸው ሕጎች ለባለአክሲዮኖች የተከበሩ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን የሚከተሉት መብቶች አሉት።

10.1 በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የመገኘትና የመሳተፍ፣

10.2 በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚፈቀደውን የትርፍ ድርሻ የማግኘት፣

10.3 በሕግ ድምጽ የመስጠት መብትን የሚያሳጡ ሁኔታዎች ከሌሉ በስተቀር በያዘዉ በእያንዳንዱ አክሲዮን አንድ ድምጽ የመስጠት፣

10.4 በሕግ የተቀመጠዉ የአክሲዮን ባለቤትነት መጠን ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ገንዘብ/ካፒታል ለማሳደግ አዲስ አክሲዮኖች በሚወጡበት ጊዜ አስቀድሞ በያዛቸው አክሲዮኖች መጠን/ስሌት ልክ አዲስ አክሲዮኖችን በቅድሚያ የመግዛት፤

10.5 ቃለ-ጉባዔዎችን እና ጠቅላላ ስብሰባዎች ላይ የተገኙ አባላትን ስም ዝርዝር የመመልከት፤

10.6 የሀብትና ዕዳ ሒሳብ፣ የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ እና የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርቶች ቅጅዎችን የመመልከትና የመውሰድ፤

10.7 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰር ወይም በሌላ ምክንያት ሥራ በሚያቆምበትና ንብረቱ በሚጣራበት ጊዜ ለካፒታል ባስገባው መዋጮ መጠን ተሰልቶ ከተጣራው ንብረት ላይ ድርሻውን የማግኘት፤

አንቀጽ አሥራ አንድ
ለባንኩ ዕዳ የባለአክሲዮኖች ተጠያቂነት

የባለአክሲዮኖች ኃላፊነቶች በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍና አግባብነት ባላቸው ሕጐች ድንጋጌዎች መሠረት የሚወሰን ሲሆን ባለአክሲዮኖች ለአክሲዮን ማህበሩ ዕዳ ወይም አክሲዮን ማህበሩ ለገባቸዉ ግዴታዎች ተጠያቂ የሚሆኑት በስማቸው በያዟቸው አክሲዮኖች ዋጋ መጠን ልክ ብቻ ይሆናል፡፡

አንቀጽ አሥራ ሁለት
የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች መብትና ኃላፊነት

12.1 ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች አክሲዮን በጋራ መግዛት ይችላሉ፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ የባለአክሲዮንነት መብታቸውን የሚጠቀሙት የጋራ ወኪል በመሾም ነው፡፡

12.2 የጋራ ወኪል ባልሾሙ ጊዜ አክሲዮን ማህበሩ ለአንዱ ባለአክሲዮን የጋራ ባለቤት የሚሰጠው ማስታወቂያ ወይም መግለጫ ለቀሪዎቹ የአክሲዮኑ የጋራ ባለቤቶችም ጭምር እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

12.3 የአክሲዮን የጋራ ባለቤቶች ከባለአክሲዮንነት ለሚመነጩ ግዴታዎች በአንድነትና በተናጠል ተጠያቂ ናቸው፡፡

አንቀጽ አሥራ ሶስት
በመያዣ ወይም በአላባ ስለሚሰጡ አክሲዮኖች

13.1 የተለየ ስምምነት በሌለ ጊዜ፣ አክሲዮኖች በመያዣ ወይም በአላባ ጥቅም የተሰጡ እንደሆነ፤ በአክሲዮን ማህበሩ ጉባዔዎች ድምፅ የመስጠት መብት የሚኖረው አክሲዮኑን በመያዣ የያዘው ወይም የአላባ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

13.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት ለነባር ባለአክሲዮኖች አዲስ አክሲዮን በቅድሚያ የመግዛት መብት የባለአክሲዮኑ ሆኖ ይቀጥላል፡፡

13.3በመያዣ የተሰጠን የተፈረመ አክሲዮን ያልተከፈለ ቀሪ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የባለአክሲዮኑ ሲሆን በአላባ ጥቅም የተሰጠን የተፈረመ አክሲዮን ያልተከፈለ ቀሪ ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት የአላባ ጥቅም ያለዉ ሰዉ እና ባለአክሲዮኑ ናቸዉ፡፡

13.4የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በመያዣ ወይም በአላባ ጥቅም የተሰጠ አክሲዮን የሚያስገኘዉን ትርፍ የሚቀበለዉ መያዣ ተቀባዩ ወይም የአላባ ጥቅም ያለዉ ሰዉ ነዉ፡፡

አንቀጽ አሥራ አራት
አክሲዮኖችን ለሌላ ወገን ስለማስተላለፍ

14.1. አክሲዮኖች ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ያለምንም ገደብ ይተላለፋሉ፡፡

14.2. አክሲዮኖች ለሌላ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ ይኸው ሁኔታ በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ መጻፍ ያለበት ሲሆን በባለአክሲዮኖች መዝገብ ላይ ካልተጻፈ በስተቀር መብቱ ለተላለፈለት ሰው የተሟላ ሆኖ አይቆጠርም፤ የአክሲዮን ዝውውሩም ዋጋ አይኖረውም፡፡

14.3. አክሲዮኖች በጋራ ከያዙ ባለአክሲዮኖች መካከል አንዱ ቢሞት የሟች የአክሲዮን ድርሻ ላይ መብት የሚኖራቸው በሕይወት የሚገኘው (የሚገኙት) የሟቹ ወራሽ /ወራሾች/ ይሆናሉ፡፡

አንቀጽ አሥራ አምስት
ባንኩ ስለሚይዛቸዉ መዝገቦች

15.1 ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚኖሩ ሕጎች በሚያዙት መሠረት ባንኩ መዝገቦችን ይይዛል፤ መዝገቦቹ የሚኖራቸዉ ዝርዝር ይዘት አግባብ ባለዉ ሕግ ይወሰናል፤ እንደአስፈላጊነቱም ተጨማሪ ይዘት ሊኖራቸዉ ይችላል፡፡

15.2 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 15.1 የተጠቀሰዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የባለአክሲኖች መዝገብ የባለአክሲዮኖችን ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የተፈረሙ የአክሲዮኖች ብዛትና መለያ ቁጥር፣ የተከፈለ ገንዘብ መጠንና ባለአክሲዮኖቹ የተመዘገቡበት ቀን መያዝ አለበት፡፡ ከባንኩ ጋር ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ ደግሞ በአዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 311 የተመለከቱትን መረጃዎች ይያዛል፡፡

15.3ባንኩ የባለአክሲኖችን መዝገብ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን መዝገብ፣ የተገለጸ የጥቅም ግጭትን መዝገብ እና ከባንኩ ጋር ቅርበት ያላቸዉን ሰዎች መዝገብ በባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በወረቀት ወይም ለረዥም ዘመን በሚቆይ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ይይዛል፡፡

15.4 የባለአክሲዮኖችን መዝገብ እና ከባንኩ ጋር ቅርበት ያላቸዉ ሰዎች መዝገብ ማንኛውም ባለአክሲዮን እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው በነጻ ሊመለከተው ይችላል፤

15.5 ባለአክሲዮኖች እና ማንኛውም በሕግ የተፈቀደለት ሰው የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የባለአክሲዮኖችን መዝገብ ግልባጭ ወይም በአጭር የተውጣጣ ጽሑፍ እንዲሰጠው አክሲዮን ማህበሩን መጠየቅ ይችላል።

አንቀጽ አሥራ ስድስት
የአክሲዮን ማህበሩ አደረጃጀት

አክሲዮን ማህበሩ የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል።

16.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

16.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ

16.3 ፕሬዚዳንት/ዋና ሥራ አስፈፃሚ

16.4 ኦዲተሮች

16.5 የአክሲዮን ማህበሩ ፀሐፊ

አንቀጽ አሥራ ሰባት
የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ

17.1 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ የአክሲዮን ማህበሩ የሥራ አመራር የበላይ አካል ነው።

17.2 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም አስቸኳይ ጠቅላለ ጉባኤ ነዉ።

17.3 የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች በንግድ ሕጉና በዚህ የአክሲዮን ማህበሩ የመመሥረቻ ጽሑፍ መሠረት ይካሄዳል።

17.4 የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ የሚደረገዉ እንደነገሩ ሁኔታ በዳይሬክተሮች ቦርድ፣ በኦዲተሮች፣ በሒሳብ አጣሪዎች፣ በፍርድ ቤት ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠዉ ሌላ አካል ነዉ።

17.5 ባለአክሲዮኖች በጠቅላላ ጉባዔ ላይ በአካል በመገኘት ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች የተስማሙ እንደሆነ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሃሳባቸውን በጽሑፍ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በመግለጽ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ።

17.6 እንደጉባዔው ዓይነትና እንደአጀንዳዉ ጉዳይ በሕግ የሚጠየቀው ምልዓተ ጉባዔ እና የድምፅ ብልጫ መሟላት እንደተጠበቀ ሆኖ በጠቅላላ ጉባዔ የተላለፉ ውሳኔዎች በጉባዔዉ ላይ በተገኙም ሆነ ባልተገኙ፣

በሃሳብ በተለዩ፣ በውሳኔው ባልተስማሙ፣ ድምጽ ባልሰጡ ወይም ድምፅ መስጠት በማይችሉ ባለአክሲዮኖች፤ ባጠቃላይ በሁሉም ባለአክሲዮኖች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

17.7 የአክሲዮን ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ሲካሄድ በጉባኤዉ የሚመረጡ ድምፅ ቆጣሪዎች ቁጥር 3 (ሶስት) ይሆናል፡፡ የሚመረጡትም ፈቃደኛ በሆኑና ከፍተኛ ድርሻ ባላቸዉ ባለአክሲዮኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ነዉ፡፡ ከፍተኛ ባለአክሲዮኖች ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ወይም ጠቅላላ ጉባኤዉ ሌላ ሰዉ ለመምረጥ ሲወስን በጠቅላላ ጉባኤዉ የሚመረጡ ይሆናሉ፡፡

17.8 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 17.6 የተደነገገው ቢኖርም ባለአክሲዮኑ ራሱ ካልተስማማ በስተቀር ባለአክሲዮኑ በባለአክሲዮንነቱ የሚገባውን መሠረታዊ መብት ጠቅላላ ጉባዔው ሊነፍገው አይችልም፡፡

አንቀጽ አሥራ ስምንት
የጠቅላላ ጉባዔዎች የጥሪ ማስታወቂያ

18.1 ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት በሚያስፈልግበት ጊዜ የጉባዔው ጥሪ የሚተላለፈዉ ከስብሰባው ዕለት 24 (ሃያ አራት) ቀናት አስቀድሞ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም ጥሪዉ ለእያንዳንዱ ባለአክሲዮን በባንኩ ወጪ በፖስታ በሚላክ የተመዘገበ ደብዳቤ ወይም ባለአክሲዮኑ ለዚሁ ዓላማ ለባንኩ በሰጠዉ የኢሜይል አድራሻ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ይሆናል፡፡

18.2 የጥሪ ማስታወቂያው በፖስታ ወይም በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚላክ መልዕክት/ደብዳቤ በሚሆን ጊዜ ስብሰባውን በሚጠራው አካል የገዛ ውሳኔ መሠረት ጥሪው በተጨማሪ በጋዜጣ ሊደረግ ይችላል፡፡

18.3 ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ 18.1 እና 18.2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሌላ ማስታወቂያ ለባለአክሲዮኑ የሚተላለፈዉ ባስመዘገበው አድራሻ መሠረት እንደአመቺነቱ በመልዕክተኛ፣ በፖስታ፣ በፋክስ፣ በኢሜል፣ በስልክ የጽሑፍ መልዕክት ወይም በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ሊሆን ይችላል፡፡

18.4 በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በወኪል አማካኝነት ለመሳተፍ የሚያስችል የውክልና ስልጣን አሰጣጥና አቀራረብ በጥሪ ማስታወቂያዉ ላይ ይገለጻል፡፡

አንቀጽ አስራ ዘጠኝ
የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ ጉባዔዎች

19.1 በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የሚደረጉ ውይይቶች በቃለ-ጉባዔ መያዝ አለባቸው፡፡ ቃለ-ጉባዔዎቹ በስብሰባው ላይ በተገኙት ዳይሬክተሮች እና በማህበሩ ፀሐፊ ይፈረማሉ፡፡

19.2 ቃለ-ጉባዔ ወደ ቃላ ጉባኤ መዝገብ በትክክል ስለመገልበጡ በአክሲዮን ማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢ ወይም በሌሎች ሁለት የቦርድ አባላት መረጋገጥ አለበት፡፡

19.3 የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎች በተለይ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች መያዝ አለባቸው፡፡

19.3.1 የጉባዔውን ጥሪ አደራረግ፤

19.3.2 የስብሰባውን ቦታና ቀን፤

19.3.3 አጀንዳዎቹን፤

19.3.4 በጉባዔው የተገኙና ያልተገኙ የቦርድ አባላትን ስም፤

19.3.5 በስብሰባው ላይ የተገኙ የአክሲዮኖች ብዛትና የምልዓተ ጉባዔው ቁጥር፤

19.3.6 ለጉባዔው የቀረቡ ሠነዶችን፤

19.3.7 የውይይቱን አጭር ማጠቃለያ፤

19.3.8 የተሰጡትን ድምጾች ውጤት እና

19.3.9 ጉባዔው ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች፤

አንቀጽ ሃያ
የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔየሚደረግበት ጊዜ

መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኦዲተሮች በሚያደርጉት ጥሪ መሠረት በዓመት አንድ ጊዜ የበጀት ዓመቱ በተዘጋ በስድስት ወራት ውስጥ መደረግ አለበት፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔዎች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ ሃያ አንድ
የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

በንግድ ሕጉና አግባብነት ባላቸው የባንክ ሥራ ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ እንደአስፈላጊነቱ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል::

21.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን ይሰይማል፣ ይሽራል፣ ክፍያቸውን ይወስናል፡፡

21.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፤ይሽራል፤

21.3 የባንኩን የሀብትና ዕዳ ሂሳብ፣ የትርፍና ኪሣራ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት፣ የኦዲተሩን ሪፖርት አድምጦ የማሻሻል ወይም የማጽደቅ፣ ወይም ያለመቀበል፣ በትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል እንዲሁም በአጠቃላይ ያለፈው የሂሳብ ዓመት ማጠቃለያን የተመለከቱ የሂሳብ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፡፡

21.4 የባንኩን ኦዲተር ይሰይማል፤ ይሽራል፤ የሥራ ጊዜውንና የሚከፈለውን ክፍያ ይወስናል፤

21.5 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲወስንባቸው ተለይተው ከተቀመጡት ጉዳዮች ውጭ ባሉ ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

አንቀጽ ሃያ ሁለት
መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ ስለሚተላለፍበት ድምጽ

22.1 በመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የመጀመሪያ ጥሪ፣ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸዉ አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ (1/4) የያዙ ባለአክሲዮኖች ራሳቸው ወይም እንደራሴዎቻቸው መገኘት አለባቸው።

22.2 በሁለተኛው ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸዉ አክሲዮኖች የትኛውንም ያህል የያዙ ባለአክሲዮኖች ከተገኙ፣ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል።

22.3 ድምጸ ተአቅቦዎችን እና ባዶ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ከግምት ውጭ በማድረግ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የሚጸድቁት ጉባዔው ላይ ከተገኙት በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

አንቀጽ ሃያ ሶስት
የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

በንግድ ሕጉ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጐች ውስጥ የተደነገገው የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጠቃላይ ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣኖች ይኖሩታል።

23.1 የባንኩን የመመሥረቻ ጽሑፍ ማሻሻል፤

23.2 የባንኩን ዓላማዎች ማሻሻል ወይም መቀየር፤

23.3 የባንኩ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) እንዲያድግ ወይም እንዲቀንስ መወሰን፤

23.4 ባንኩ እንዲፈርስና ሂሳቡም እንዲጣራ መወሰን፤

23.5 ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ባንኩ ሌላ ተቋም/ድርጅት እንዲጠቀልል ወይም እንዲገዛ፤ ከሌላ ተቋም/ድርጅት ጋር እንዲዋሀድ፤ በሌላ ተቋም/ድርጅት እንዲጠቀለል/እንዲገዛ ወይም እንዲከፋፈል መወሰን፤

አንቀጽ ሃያ አራት
አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ለማካሄድ ስለሚያስፈልገው ምልዓተ-ጉባዔ እና ውሳኔ ስለሚተላለፍበት ድምጽ

24.1 የባንኩ ዜግነት እንዲለወጥ ወይም በነባር አክሲዮኖች ላይ የተጻፈውን ዋጋ በመጨመር የባንኩ ካፒታል ከፍ እንዲደረግ የሚጠይቁ ውሳኔዎች ዋጋ ሊኖራቸው የሚችለው ድምጽ ለመስጠት መብት ያላቸውን አክሲዮኖች የያዙ ባለአክሲዮኖች በአስቸኳይ ጉባዔው ላይ ተገኝተው ወይም ተወክለው በሙሉ ድምፅ ሲስማሙ ብቻ ይሆናል።

24.2 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 24.1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉንም አስቸኳይ ጉባዔ ማካሄድ የሚቻለዉ፡-

24.2.1በመጀመሪያ የጉባዔ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ ሶስተኛ (1/3) የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

24.2.2በሁለተኛ የጉባዔ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አክሲዮኖች ቢያንስ አንድ አራተኛ (1/4) የያዙ ባለአክሲዮኖች ሲገኙ ወይም ሲወከሉ፣

24.2.3በሦስተኛ የጉባዔ ጥሪ ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸዉ አክሲዮኖች የትኛዉንም ያህል የያዙ ባለአክሲዮኖች ከተገኙ ጉባዔው ስብሰባውን ለማካሄድና ውሳኔ ለማስተላለፍ ይችላል፡፡

24.3 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 24.1 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም አስቸኳይ ጉባዔ ላይ ውሳኔዎች በጉባኤዉ ላይ ከተገኙት በሁለት ሶስተኛ (2/3ኛ) አብላጫ ድምጽ ይተላለፋሉ፡፡ ለድምጽ ብልጫው አቆጣጠር ስሌት ድምጽ ያልሰጡም ሆነ ድምጽ ያልተጻፈባቸው የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ግምት ውስጥ አይገቡም፡፡

አንቀጽ ሃያ አምስት
የዳይሬክተሮች ቦርድ

25.1 ሹመት፣ብዛትና የአገልግሎት ዘመን

25.1.1 የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር 9 (ዘጠኝ) ነዉ፤ የሚመረጡትም በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሆናል፡፡ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚኖረዉ ሕግ መሠረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

25.1.2የዳይሬክተሮች የሥራ ዘመን 3 (ሦስት ዓመት) ነዉ፡፡ አንድ ዳይሬክተር ለሁለተኛ የሥራ ዘመን መመረጥ የሚችል ሲሆን ከስድስት ተከታታይ ዓመታት ወይም ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ በዳይሬክተርነት ማገልገልንና ከዚያ በኋላ እንደገና መመረጥን በተመለከተ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚኖረዉ ሕግ መሠረት የሚወሰን ይሆናል።

25.1.3ጠቅላላ ጉባዔው በሕጉ እና በዚህ መመሥረቻ ጹሑፍ በተገለፀው መሠረት ዳይሬክተሮችን በማናቸውም ጊዜ የማሰናበት ሥልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከጠቅላላ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ከ50% በላይ የሚሆኑት ዳይሬክተሮች የሥራ ዘመናቸዉ ከመጠናቀቁ በፊት የሥራ ስንብት ካቀረቡ አዲስ ምርጫ ይካሄዳል፡፡

25.1.4ሥራቸዉን የሚለቁ ዳይሬክተሮች ሥራቸውን ማቋረጥ ወይም አዲስ ለተመረጡት ዳይሬክተሮች ማስተላለፍ የሚችሉት የአዲሶቹ ምርጫ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አግኝቶ ሹመታቸዉ

በፅሑፍ ከጸደቀ በኋላ ሲሆን በአዲስ ተመራጭ ዳይሬክተሮች እስከሚተኩ ድረስ ሳያቋርጡ ባንኩን የማገልገል ግዴታ አለባቸው።

25.2 ሥልጣንና ተግባር

አግባብነት ባላቸው ሕጎች፣ በባንኩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር የመፈፀም ግዴታ አለበት።ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል።

25.2.1የአክሲዮን ማህበሩን ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣የውስጥ ኦዲት ኃላፊና የሪስክና ኮምፕሊያንስ ኃላፊ ይመርጣል፤

25.2.2የዋና ሥራ አስፈፃሚዉ ምክትል የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎችን (ሲኒየር ኤክስኪዩቲቭ ኦፊሰሮችን) በዋና ሥራ አስፈፃሚዉ ተመርጠው ሲቀርቡለት ሹመታቸውን ያጸድቃል።

25.2.3በዋና ሥራ አስፈፃሚዉ በሚቀርብለት መሰረት የአክሲዮን ማህበሩን ጸሐፊ ቅጥርና ስንብት በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፤

25.2.4የአክሲዮን ማህበሩን የረጅም ጊዜ ስትራቴጂ፣ ፖሊሲዎች፣ የአደረጃጀት መዋቅርና የደመወዝ ስኬል በዋና ሥራ አስፈፃሚው ተዘጋጅተው ሲቀርቡለት መርምሮ ያጸድቃል።

25.2.5ተቀጥላ ማቋቋምን እና ከኢትዮጵያ ውጪ ቅርንጫፍ መክፈትን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል፤

25.2.6በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚቀርቡለትን የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ያጸድቃል።

25.2.7 የማይንቀሳቀሱ ወይም የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን የመሸጥ ጉዳዮች ላይ ይወስናል።

25.2.8 ሊሰበሰቡ የማይችሉ ብድሮችንና ሌሎች ተሰብሳቢ ክፍያዎችን መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መርሆችን በመከተል ከሂሳብ መዝገብ ላይ ይሰርዛል፤እንዲሁም አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ቋሚ ንብረቶችን ከመዝገብ ላይ ይሰርዛል።

25.2.9የባንኩን የማይንቀሳቀሱም ሆነ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶች በዋስትና በማስያዝ ወይም ያለምንም ዋስትና በባንኩ ስም ይበደራል።

25.2.10 የባንኩን ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፤ ይመራል፤

25.2.11 ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤

25.2.12 የጠቅላላ ጉባኤዉንና የቦርዱን ቃለ ጉባኤዎች፣ የባንኩን የሒሣብ መዛግት እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፤

25.2.13 በሕግ እና በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ያቋቁማል፣ ይይዛል፤

25.2.14 የራሱን የአሠራር ደንብ ሊያዘጋጅ ይችላል፤

25.2.15 ከአባላቱ መካከል ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ይመርጣል፡፡

25.2.16 እንደአስፈላጊነቱ ሥልጣኑን ለቦርዱ ኮሚቴ ወይም ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ሊሰጥ ይችላል፡፡

25.3 የቦርድ ስብሰባዎች

25.3.1 የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና ጽ/ቤት ወይም ሰብሳቢው በሚመርጠው በሌላ ቦታ ቢያንስ በሶስት ወር 1/አንድ/ ጊዜ ይሰበሰባል፤ከዚህም ሌላ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ ስብሰባዎች ሊያካሄድ ይችላል፡፡

25.3.2የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ሰብሳቢዉን ተክቶ ይሰራል፡፡ ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ ከቀሩት የቦርድ አባላት መካከል በቦርዱ ውስጥ ከፍተኛ የአገልግሎት ዘመን ያለዉ ቦርዱን ይመራል፤ ከፍተኛ አገልግሎት ያለዉ የቦርድ አባል ከሌላ በቦርዱ የሚሰየም የቦርድ አባል ቦርዱን ይመራል፡፡

25.3.3የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስብሰባ የሚያካሄዱት በስብሰባዉ ላይ ራሳቸዉ በአካል በመገኘት ወይም በተወካይ አማካኝነት ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመሳተፍ ነዉ፡፡ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚደረግ የቦርድ ስብሰባ ላይ ሁሉም ወይም የተወሰኑ የቦርድ አባላት በአካል መገኘት ሳይጠበቅባቸዉ ስብሰባ ማድረግና በማናቸዉም በቦርድ ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ጉዳይን በተመለከተ ውሳኔ ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ቦርዱ በሚያወጣዉ የአሠራር ደንብ ውስጥ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ በሚደረግ ስብሰባ ውሳኔ የሚሰጥበትን ወይም የማይሰጥበትን ጉዳይ ለይቶ ሊያስቀምጥ ይችላል፡፡

25.3.4ከጠቅላላው ዳይሬክተሮች ቁጥር 51% (ሃምሣ አንድ በመቶ) የሚሆኑት በስብሰባው ላይ በራሳቸው ወይም በወኪላቸው ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ካልተገኙ በስተቀር ቦርዱ ውሳኔ ማሳለፍ አይችልም፡፡ ውሳኔ የሚተላለፈው በድምጽ ብልጫ ነው፡፡ ድምጹ እኩል ለእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሃሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

25.3.5በቦርድ ስብሰባ ለመገኘት የማይችል ዳይሬክተር የሚወከለው በሌላ ዳይሬክተር ብቻ ይሆናል፡፡ በአንድ ስብሰባ ላይ አንድ ዳይሬክተር ሊወክል የሚችለው አንድ ዳይሬክተርን ብቻ ነው፡፡

25.4 ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

25.4.1 የዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 25.1.1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ በሂሳብ ዘመኑ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ዳይሬክተሮች ከቦርድ አባልነት የለቀቁ ወይም የተገለሉ እንደሆነ ያሉት ዳይሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚተኩ ሌሎች ዳይሬክተሮችን ይሰይማሉ፡፡

25.4.2 በማናቸውም ጊዜ የቦርድ አባላት ብዛት ከ50% በታች የቀነሰ እንደሆነ የቀሩት አባላት ተተኪዎች ለማሾም አባላቱ ከጐደሉበት ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ጠቅላላ ጉባዔ መጥራት አለባቸው፤ በጐደሉት አባላት ምትክ ሹመት እስኪደረግ ድረስ የቀሩት አባላት ባንኩን ያስተዳድራሉ።

አንቀጽ ሃያ ስድስት
የዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ኃላፊነቶች

26.1 ባንኩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ይኖረዋል። የዋና ሥራ አስፈፃሚው ተጠሪነት ለቦርድ ሆኖ ደመወዙና ጥቅማ ጥቅሙ በቦርዱ ይወሰናል።

26.2 ዋና ሥራ አስፈጻሚዉ የአክሲዮን ማህበሩን ጠቅላላ የዕለት ተዕለት ሥራ በበላይነት የመምራት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት የአክሲዮን ማህበሩ ተወካይና ተጠሪ ሆኖ ይሰራል።

26.3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 26.2 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

26.3.1በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ የተመለከቱትን ዓላማዎች ለማሟላት በባንኩ ስም እና ባንኩን ወክሎ ይሰራል፤

26.3.2 ባንኩ በዓለም አቀፍ እና በሀገር ውስጥ ከሚያካሄዳቸው ሥራዎች ጋር በተያያዘ በሦስተኛ ወገኖች፣ በመንግሥታት፣በሕዝባዊ ተቋማት፣ በግል ድርጅቶች፣ በባንኮች እና በሌሎች የገንዘብ ተቋማት ዘንድ ባንኩን ይወክላል፤

26.3.3የአክሲዮን ማህበሩን የሥራ ዕቅድ፣ የረዥም ጊዜ ስትራቴጂና ፖሊሲዎች አዘጋጅቶ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

26.3.4 የባንኩን የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶች እና የውስጥ የማኔጅመንት መመሪያዎች (procedures and guidelines) ያጸድቃል፤

26.3.5 የባንኩን የአደረጃጀት መዋቅር (organizational structure) አዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለቦርድ ያቀርባል፤ ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

26.3.6 ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠሪ የሆኑ ከፍተኛ ሥራ አስፈፃሚዎችን (ኃላፊዎችን) ይመርጣል፤ ለቦርድ በማቅረብ ሹመታቸውን ያስጸድቃል፤

26.3.7 የባንኩን የሂሳብ አያያዝ በሚመለከት አመራር ይሰጣል፤ ተገቢውን ቁጥጥር ያደርጋል፤

26.3.8 በሕጉ፣ በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ እና በባለአክሲዮኞች ጉባኤ በሚወሰነዉ መሠረት የመጠባበቂያ ሒሣብ እና ሌሎች የመጠባበቂያ ሒሳቦችን ያቋቁማል፤

26.3.9 ቼኮችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተስፋ ሠነዶችን፣ የሐዋላ ወረቀቶችን፣ ሌሎች የሚተላለፉ ሠነዶችን እንዲሁም የገቢና ወጪ ንግድ ሰነዶችን ያወጣል፣ ይፈርማል፣ ይቀበላል፣ያጸድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል፤

26.3.10 ቦርዱ ሲፈቅድ የአጭር ጊዜም ሆነ የረዥም ጊዜ ብድሮችን ይበደራል፤ ሆኖም ከባንኮች የገንዘብ ገበያ (interbank money market) እና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሚወስዳቸዉ ብድሮች ቦርዱን ማስፈቀድ ሳያስፈልገዉ መበደር ይችላል።

26.3.11 ሹመታቸዉ በቦርድ ከሚጸድቅላቸዉ ኃላፊዎች በስተቀር የሠራተኞችን ቅጥር፣ ዕድገት፣ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፣ ማሰናበት፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅማቸዉን በተመለከተ ይወስናል፤

26.3.12 በባንኩ የኢንቨስትመንት ፖሊሲ መሠረት በሥራ ላይ ያልዋለን ገንዘብ ኢንቨስት ያደርጋል ወይም በአትራፊ ሥራ ላይ ያውላል፤

26.3.13 ባንኩ ባለድርሻ በሆነባቸዉ ድርጅቶች ውስጥ ባንኩን ወክሎ በመመስረቻ ፅሑፍ ላይ ይፈርማል፣ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በመገኘት ድምፅ ይሰጣል፣ በቃላ ጉባኤ ላይ ይፈርማል፤

26.3.14 በባንኩ ስም በማናቸውም ባንኮች የባንክ ሂሳብ ይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፣ ይዘጋል፤

26.3.15 በባንኩ ስም ንብረት ይከራያል፣የባንኩን ንብረት ያከራያል፣ የኪራይ ውል ይፈርማል።

26.3.16 በባንኩ ፖሊሲ መሠረት በባንኩ ስም ንብረት ይገዛል፣ ይሸጣል፣ ያስተላልፋል።

26.3.17 የባንኩን ዓመታዊ የሥራ እንቅስቃሴ የሚመለከት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ያቀርባል፤

26.3.18 ለባንኩ የዕለት ከዕለት ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ሕጋዊ ወጪዎችንና ክፍያችን ይፈቅዳል፤

26.3.19 የባንኩን ጥቅም ለመጠበቅ ለጠበቃ የውክልና ሥልጣን ይሰጣል፣ ወኪሎችን ይሾማል፣ ሌሎች ውክልናዎችን ይሰጣል፣ ውክልናቸዉን ይሽራል፣ ለአገልግሎታቸዉ የሚከፈለዉን ይወስናል፤

26.3.20 የተሰጠዉን ሥልጣን ተግባራዊ ለማድረግ ባንኩን በመወከል ከሶስተኛ ወገን ውል ይፈራራማል፤ ባንኩን ወክሎ ይሠራል፤

26.3.21 በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ከተሰጡት ሥልጣኖች የተወሰነዉን ለባንኩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤

26.3.22 በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትንና ውሳኔዎችን ያስፈፅማል፤

አንቀጽ ሃያ ሰባት

የውጭ ኦዲተሮች ሹመት፣ ኃላፊነትና ተግባር

27.1 የባንኩ የውጭ ኦዲተር በባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይሾማሉ። ሆኖም ሹመቱ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መጽደቅ አለበት። የአገልግሎት ዘመናቸዉ ለሶስት ዓመት ይሆናል።

27.2 የውጭ ኦዲተር ተግባርና ኃላፊነት በንግድ ሕግ፣ በባንክ ሥራ አዋጅ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች እና ሌሎች ሕጎች የተጠቀሱት ይሆናል፡፡

27.3 በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 27.2 ሥር የተጠቀሰዉ ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ኦዲተሮች፡-

27.3.1 በየዓመቱ የባንኩን የሒሣብ ሰነዶች መመርመርና ትክክለኛ ስለመሆናቸዉ ማረጋገጫ መስጠት፣

27.3.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ ለጠቅላላ ጉባኤ በሚያቀርበዉ ሪፖርት እና በባንኩ የሒሣብ መዛግብት ላይ ያላቸዉን አስተያየት ለጉባኤዉ ማቅረብ

አንቀጽ ሃያ ስምንት
የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ ሹመት፣ ሥልጣንና ተግባር

የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ በዋና ሥራ አስፈፃሚው አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ ይሾማል፡፡ የአክሲዮን ማህበሩ ጸሐፊ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

28.1 የባንኩን መረጃዎችና መዛግብት የማደራጀትና የመያዝ፣

28.2 ለሚመለከታቸዉ አካላት ሪፖርቶችንና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን በወቅቱ የመስጠት፣

28.3 የባለአክሲዮኖችንና የዳይሬክተሮች ቦርድን ስብሰባዎች የማዘጋጀት፤

28.4 የጠቅላላ ጉባኤ እና የቦርድ ፀሐፊ ሆኖ የመስራት፣ ቃለ-ጉባዔዎችን የማዘጋጀትና አደራጅቶ የመያዝ፤

28.5 አግባብነት ባላቸዉ የመገናኛ ዘዴዎች የቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ መመዘኛዎችን የማሳወቅ፣

28.6 በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የማከናወን እና

28.7በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ የአክሲዮን ማህበር ጸሐፊ ሥልጣንና ተግባርን የመፈጸምና የማስፈጸም፡፡

አንቀጽ ሃያ ዘጠኝ
የሒሣብና የፋይናንስ መዝገቦችና መረጃዎች

29.1 ባንኩ አግባብነት ያላቸውን ሕጐች በመከተል የሂሳብ መዝገብ ይይዛል፣ ይመዘግባል፡፡

29.2 ባንኩ አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት የባንኩን የሥራ እንቅስቃሴ እና ያለውን የገንዘብ አቋም በግልጽና በትክክል የሚያስረዱ መዝገቦችን በአግባቡ ይይዛል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ
የአክሲዮን ማህበሩ የሂሳብ ዓመትና ሪፖርት

30.1 የአክሲዮን ማህበሩ የሂሳብ ዓመት እ.ኤ.አ ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ በሚቀጥለው ዘመን ሰኔ 30 ያበቃል፡፡

30.2 የዳይሬክተሮች ቦርድ በእያንዳንዱ የሂሳብ ዘመን ማብቂያ ላይ የባንኩን የሀብትና ዕዳ ሒሣብ፣ የትርፍ እና ኪሣራ መግለጫ፣ የዳይሬክተሮች ቦርድንና የኦዲተሮችን ክፍያ እና ያለፈዉን ዓመት የባንኩን ሁኔታና እንቅስቃሴ የሚያሳይ መግለጫና ሪፖርት አዘጋጅቶ ለባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አንድ
የመጠባበቂያ ገንዘብ

ባንኩ በየጊዜዉ በሚኖረዉ ሕግ መሠረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፣ ያስቀምጣል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ ሁለት
የትርፍ ክፍፍል

32.1 አግባብነት ባላቸዉ ሕጎች መሠረት ከተገኘዉ ጠቅላላ ትርፍ ላይ መቀነስ ያለባቸዉ ሒሣቦች መቀነሳቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የትርፍ ክፍፍል የሚፈፀመው የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያቀርበዉ የውሳኔ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚሰጠዉ ውሳኔ መሠረት ነው፡፡

32.2 የባለአክሲዮኖች የትርፍ መጠን የሚሰላው በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ ባላቸዉ የተከፈለ ካፒታል መጠንና የተከፈለዉ ካፒታል በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተከፈለበት ጊዜ ግምት ውስጥ ገብቶ ነው፡፡

አንቀጽ ሰላሳ ሶስት
ስለምዝገባና ሪፖርቶችን ይፋ ስለማድረግ

33.1 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ ላይ የሚደረግ ማናቸውም ማሻሻያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀ በኋላ አግባብ ባለው ሕግ በተደነገገው መሠረት ይመዘገባል፡፡

33.2 የአክሲዮን ማህበሩ በውጭ ኦዲተሮች የተረጋገጠ የሀብትና ዕዳ ሒሣብ እና የትርፍና ኪሳራ መግለጫ በባንኩ ድረ-ገፅ ላይ እንደወጣ ይደረጋል፤ እንደሁኔታዉ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራጭ ጋዜጣ እንዲታተም ሊደረግ ይችላል፡፡

አንቀጽ ሰላሳ አራት
የአክሲዮን ማህበሩን ለማፍረስ የሚያበቁ ምክንያቶች

34.1 የአክሲዮን ማህበሩ አግባብ ባለው ሕግ በተመለከተዉና በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፡፡

34.2 ከሚከተሉት ምክንያቶች ውስጥ ማናቸውም ቢሆን ለአክሲዮን ማህበሩ መፍረስና ሂሳብ ማጣራት በቂ ሆኖ ይቆጠራል፡፡

34.2.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዓላማ ተግባራዊ ሳይሆን ሲቀር ወይም አክሲዮን ማህበሩ ተግባሩን ለማከናወን ከአቅሙ በላይ የሆኑ ምክንያቶች ሲያጋጥሙት፤

34.2.2 አክሲዮን ማህበሩ በፈቃደኝነት እንዲፈርስ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሲወሰን፤

34.2.3 ፍ/ቤት አክሲዮን ማህበሩ የሚፈርስበት በቂ ምክንያት መኖሩን በማረጋገጥ እንዲፈርስ ትዕዛዝ ሲሰጥ፤

34.2.4 አክሲዮን ማህበሩ በመክሰሩ ምክንያት የዕዳ ማጣራትና የኪሳራ ፋይል ሲከፈት፤

34.2.5 የዋና ገንዘቡን ሦስት አራተኛ በኪሳራ ሲያጣ፤

አንቀጽ ሰላሳ አምስት
አክሲዮን ማህበሩ በሥራ የሚቆይበት ጊዜ

አክሲዮን ማህበሩ የተቋቋመው ላልተወሰነ ጊዜ ነው።

አንቀጽ ሰላሳ ስድስት
የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

በቁጥር ቅ10/249/4ሀ/2013 በ14/11/2013 ዓ.ም በተመዘገበ የባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና በ28/01/2013 ዓ.ም. በተደረገ የባንኩ የፈራሚዎች ጉባኤ ቃለ ጉባኤ ላይ ለአክሲዮን ማህበሩ አደራጆች እና መስራቾች ስለሚከፈል የትርፍ ድርሻ የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነታቸዉ ለቀሪ ሁለት ዓመታት እንዲቀጥል ተወስኗል።

አንቀጽ ሰለሳ ሰባት
የተሻሩ ሠነዶች

37.1 በአንቀፅ 36 ሥር የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በቁጥር ቅ10/249/4ሀ/2013 እና ቅ10/250/4ሀ/2013 በተመሳሳይ ቀን በ14/11/2013 ዓ.ም እንደቅደምተከተላቸዉ የተመዘገቡት የባንኩ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ የተገለፁት ድንጋጌዎች እንዲሻሩ ተወስኗል።

37.2 በቁጥር ቅ12/3018/4ለ/2014 በ14/07/2014 ዓ.ም. በተመዘገበ የባለአክሲዮኖች 1ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔ የተደረጉት የመመሥረቻ ጽሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያዎችን የሚመለከተው የውሳኔ ክፍል ተሽሮ በዚህ ሠነድ እንዲተካ ተወስኗል።

አንቀጽ ሰላሳ ስምንት
ልዩ ልዩ ጉዳዮች

38.1 ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በማናቸውም ጊዜ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ሊሻሻል ይችላል።

38.2 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ እና አግባብነት ባላቸው አስገዳጅ ሕጐች መካከል ተቃርኖ ወይም ልዩነት ሲኖር አግባብነት ያላቸው ሕጐች ተፈጻሚ ይሆናሉ። በዚህ መመሥረቻ ጽሑፍ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ቢኖሩ በንግድ ሕጉና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጐች መሠረት ይታያሉ።

38.3 በዚህ የመመሥረቻ ጽሑፍ የአማርኛው ቅጂና የእንግሊዘኛው ቅጂ መካከል የትርጉም ልዩነት ወይም ተቃርኖ የተፈጠረ እንደሆነ የአማርኛው ቅጂ ተፈፃሚ ይሆናል።

38.4 ይህ የመመሥረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ከጸደቀ በኋላ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ሲያገኝ እና በሚመለከተው አካል ሲመዘገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፤ ተፈጻሚ መሆን ይጀምራል።

------------//------------